# <u>የተቃዋሚ ሀይሎች ራዕይ አልባ አይደሉም</u>

<u>ወልዱ ስሉስ ከኮምቦልቻ</u>

ወያኔና አጫፋሪዎቹ ልዩ ልዩ ምክንያቶችን በመደርደር ተቃዋሚ ሀይሎችን ለማግለል ያደረጉት ሁሉ ምስጢር አይደለም። በደርግ ውድቀት ዋዜማ በአሜሪካኖች በተደረገው የሎንዶን ስብሰባ ወያኔ ሀቀኛ ተቃዋሚዎች በስብሰባው እንዳይገኙ ያቀረበው ምክንያት እነ ኢሕአፓ ትጥቅ ትግል አያካሄዱም የሚል ነበር። እውነቱ ይነገር ከተባለ በዚያን ወቅት ኢሕአፓ የነበረው ሀይልና ለምሳሌ ኦነግ የነበረው ታጣቂ ቁጥር እኩል አልነበረም። ነገር ግን ወያኔም ሻዕቢያም ኦነግ በድርድሩ ሌንጮ ለታ ራሱ እንዳለው በአዳማቂነት እንዲገኝ ተደረገ። በዚህ ረገድ ለምሳሌ በቅርቡ ምክትል መቶ አለቃ ታደሰ ቴሌ ሳልቫኖ በፃፈው “የአናብስት ምድር” መፅሀፍ ውስጥ ኦነግ ወደ 7ሺ ታጋይ ነበረው የተባለው የተሳሳተ ነበር። ወያኔና ሻዕቢያ ኦነግን የፈለጉት ለሽፋን ነበር፣ኢዴሀቅንም ያገለሉት ኢትዮጵያዊ በመሆኑ ችግር ፈጣሪ ይሆናል በሚል ነበር። ሳይውል ሳያድር ግን የሽግግር መንግስት ምስረታ ጉባዔ ሲጠሩ ደግሞ ኢሕአፓም ኤዴሃቅም ባለጦርና ፀረ ሰላም ተብለው ተፈረጁ።

ወያኔና አጫፋሪዎቹ ተቃዋሚ ሃይሎችን ሲከሱ ራዕይ የላቸውም ይላሉ። የሚያቀርቡት ሌላ አማራጭ የለም፣ አገዛዙ ከማብጠልጠል ሌላ ራዕይ የላቸውም ይላሉ። መለስ ዜናዊ ሲቀናጣ እንዲያውም የረባ ተቃዋሚ አጣሁ ብሎ ለማማረር ሲለፍፍ ተደምጧል። አምባገነኖች በዚህ መልክ ሲመፃደቁ ያየነው ነው። ወያኔ ተቃዋሚው ራዕይ የለውም ሲል ሌሎች ደግሞ የነቁ የበሰሉ እየመሰላቸው ይህንኑ ያስተጋባሉ፣ ድርጅቶች የሚጓዙበትን በተመለከተ ካርታ /ሮድማፕ/ የላቸወም ብለውም ይተቻሉ። ይህ ግን ከባድ ስህተት ነው። “ጥነ” ዎቹ ወይም ጥራዝ ነጠቆቹ የተባለን ከመድገም በስተቀር ሌላ እያሉ አይደለም። ተቃዋሚ ሀይሎች በአብዛኛው የየራሳቸው ሆነ የጋራ ራዕይ አላቸው። በቅድሚያ ግን ራዕይ ስንል ምን ማለት እንደሆነ መስማማት ያሻል። ራዕይ ስንል ከመለስ ቅዠት በመለስ ነገን በተመለከተ ይህ እንዲሆን እንፈልጋላን ብለን የምናምንበትን የሚጠቁም ነው። ራዕያቸው ለሕዝብ ይበጃል አይበጅም ማለት ቢቻልም ተቃዋሚ ድርጅቶች ከሞላ ጎደል የየራሳቸው ፕሮግራም አላቸው። የፖለቲካ ፕሮግራም ዕቅድን፣ ፍላጎትን፣ እምነትን የሳያል፣ ይጠቁማል። በእርግጥ አንዳንዶች በፕሮግራማቸው ድንቅ ራዕይ ያስቀምጡና አያምኑበትም። ይህ እንዳለ ሆኖ ድርጅቶች ፕሮግራም ካወጡና በዚህ እናምናለን ካሉ ይህ ራዕያቸው ነው፣ አማራጫቸው ነው። ይህን ፕሮግራም በስራ ለማዋል ወይም ለድል ለመብቃት ደግሞ ሁሉም ይለያይ ይግጠም የየራሳቸው የትግል ጎዳናና ስልት አላቸው። በብረት ወይም በሁለገብ፣ በሰላም ወይም በሕዝባዊ አመፅ፣ ከአገዛዙ ጋር ስልጣንን ለመካፈል በመጣር ወዘተ .. አንዱ ስልት ከሌላው የተሻለ ነው፣ ይበልጥ ያዋጣል ወዘተ ሊባል ቢችልም በአጠቃላይ ግን ሁሉም ድርጅት የየራሱ የጉዞ ካርታና የመድረሻው ቦታ ምንነትን በተመለከተ ግልፅ አቅዋም አለው።

ሀገር ወዳድ ተቃዋሚ ድርጅቶች የሚጋሩት ራዕይ አለ። የወያኔን አገዛዝ ለመጣል ለማስወገድ። ይህ ራዕይ የተለጣፊዎችና ከመለስ ጫማ ስር እንውደቅ የሚሉትን አይጠቀልልም። ሀገርን የማዳን ተቀዳሚ የጋራ ራዕይ በመኖሩ በዚህ መሰረት ብቻ ይህን ራዕይ የሚጋሩ ድርጅቶች ማበር መተባበር አለባቸው ማለት ትክክል ነው። ዋናው ተግባርና ግዳጅ ሀገርን ማዳን ነውና። ዝርዝር የፖለቲካ አቅዋሞች ላይ ልዩ ልዩ አመለካከት ሊኖር ቢችልም በዋናው ሀገርን በማዳን ነጥብ ላይ ስምምነት እስካለ ድርስ በዚሁ መሰረት የህብረት ግንባር መፈጠር ይኖርበታል ማለት ነው። ያሉትን ተቀዋሚ ድርጅቶች ብናያቸው ሁሉም ግልፅ ራዕይ አላቸው። አማራጭ አቅርበዋል። ወያኔ ተወግዶ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ይመስረት፣ የህዝብ አንድነት በዴሞክራሲ ላይ ይገንባ ፣ የሀገር ሉዓላዊነት ይከበር ወዘተ በሚል ቁልጭ ያለንና የተሻለን አማራጭ ተቃዋሚ ሀይሎች አቅርበዋል። ስለዚህም ተቃዋሚ ሀይሎች ራዕይ የላቸውም፣ የት እንደሚሄዱ አያውቁም፣ ያለውን አገዛዝ ይኮንናሉ እንጂ አማራጭ አያቀርቡም የሚባለው ሁሉ ሀሰት ነው። ይህን የወያኔ ሀሰት የሚያሰተጋቡ ሁሉ ሊያፍሩ ይገባቸዋል። የትግል ጉዞ ካርታው የሀገር ጎብኚ ካርታ አይደለም። የመንገድ ካርታ ወይም “ሮድ ማፕ” የላቸውም የሚባሉት ድርጅቶች ከሞላ ጎደል ግልፅ ካርታ አላቸው። የሚፈልጉትን ያውቃሉ። የሚፈልጉት ደግ ይሁን አይሁን ሌላ ጉዳይ ነው። የት

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

እንደሚሄዱና በየትም መንገድ መጓዝ እንዳለባቸውም ያውቃሉ። የመረጡት መንገድ አይወስዳቸውም ወይም ወደፈለጉት ቦታ አያደርሳቸውም ማለት ቢቻልም ቅሉ።

ድርጅቶች ራዕያቸውን ከተጨባጩ ሁኔታ ጋር አያይዘው ማስኬድ መቻል አለባቸው። ፖለቲካ ትግል ሁሌም ሲሆን በሚችል ብቻ ተብሎ የሚወሰንና የሚካሄድ አይደለም። አንድ ትልቅ አብዮታዊ መሪ ብለውት እንደነበረው የማይቻል የለም ብሎ በቁርጠኛናት መታገልን ይጠቅሳል። ስለዚህም ራዕያችን አሁን እየተለመደ በመጣው አነጋገር ይቻላልን እያስተጋባ የኢትዮጵያን ገፅታ በህዝቧ ብርታትና ትግል ለውጦ ለዜጎቿ የምታኮራ ሀገር ለማድረግ የቀለመ መሆን አለበት። ዛሬ ጭቆና በዝቶ፣ የኢትዮጵያ ህዝብና ሀገሪቷ ራሷ በህልውናቸው ላይ አደጋ ተጥሎ ቢገኝም ይህ አንድ ጠዋት ጤዛ ይተናል፣ ይወገዳል ብሎ ማመን ያስፈልጋል። በድል ላይ እምነት፣ በህዝብ አቸናፊነት ላይ እምነት ሊኖር ይገባል ማለት ነው። ህዝብ ሆ ብሎ ከተነሳ፣ ቆርጦ ከታገለ፣ አሻፈረኝ ለፀረ ህዝብ አልንበረከክም ካለና ተባብሮ ለለውጥ ካመፀ ድል አድራጊነቱ ጥርጥር የለውምና ነው። ስለሆነም ራዕያችን ከዛሬው ጨለማ ባሻገር ብርሀንን የሚያሳይና የነገን ብሩህ ቀን በህዝብ ልብ የሚያሰርፅና ለትግልም የሚያነሳሳ መሆን አለበት። ያለፈውና የገለማውን የሚመልስ ሊሆን አይቻልም። የዛሬውን ሀገር አጥፊ ቅዠትንም የሚያራዝም ሊሆን አይገባውም። ህዝብ ሲታገል ህይወቱን አሳልፎም ሊሰጥ ነውና ውድ ህይወቱን የሚገብርለት ራዕይ በእርግጥም ህዝባዊ መሆን አለበት። ሀገርን መዳን ይህ ዓይነት ክቡር ቅዱስ አላማ ነው። ግን ነገ ደግሞ በደፈናው ገበየሁ ሲሄድ ተተካ ባልቻን በአሉታዊው በማስፈን ማለትም መንግስቱ በአስከፊው መለስ የተተካው እንዳይደገም ደግሞ ለማረጋገጥ መቻል የግድ ነው። የነገ ኢትዮጵያ ዴሞክራሲ የሚሰፍንባት መሆኗ፣ ህዝቧ በእኩልነት የሚኖርባት መሆኗን ማረጋገጥና ከወዲሁ በራዕይም በሂደትም ማሳየት ያስፈልጋል። ለዚህም ነው የድርጅቶች ይዘት፣ አሰራር፣ ሀቀኛ ገፅታ መመርመሩና መታወቁ አስፈላጊ የሚሆነው። ዴሞክራሲ ያለው ሁሉ ዴሞክራሲያዊ ነው ማለት አይደለምና አስመሳዩን ከሀቀኛው መለየቱና ማወቁ ጠቃሚ ነው።

መሰረታዊው ራዕያችን ሊሆን የሚገባው የመለስ ዜናዊን አገዛዝ መደምሰስ ነው። ማስተካከል፣ መለገ፣ የጎረበጠውን ማቅናት አይደለም። ከኢትዮጵያ ገፅ ማስወገድ፣ አቸንፎ ወደ ታሪክ ትቢያ ጉድጓድ መጣል። ከዚህ በመለስ ያለ ግብ ውጤቱ ቅዠትና ሽንፈት ነው። አገዛዙ ህዝብን በብሄረሰብና በሀይማኖት እየከፋፈለ ነውናም ይህንን ለማገድ ራዕያችን ህዝብ ሳይከፋፈል የሚኖርበትን መንገድ የሚያቀርብ መሆን አለበት። መብታችን ተረገጠ የሚሉትን መብት የሚከበርበትን ራዕይ ማሳየትና የዚህም ተጋሪ እንዲሆኑ ለማድረግ መሞከር ያስፈልጋል። ፅንፈኞቹን ከህዝብ መነጠል ደግሞ ግዳጅ ነው። ብዙሀኑ አንድነትንና ሀገሩን ወዳድ ነውና ለአንድነት ጥሪ ቀና መንፈስ አለው። ያዳምጣል። አልፎ ግን የታሰበው ነገ፣ የነገይቷ ኢትዮጵያ እውነትም ለህዝቧ መብትና ክብር፣ እኩልነትና አንድነት የምትቆም፣ የምትሆን መሆኗን ሊያይ፣ ሊያምን መቻል አለበት። ትግል የችርቻሮ መድረክ ባይሆንም ህይወቱን ሊሰጥ የተነሳ ህዝብ ውድ ህይወቱን ለመስጠት ማመን አለበት። ለሀገሩ ሁሉም ህይወቱን እንደማይሰጥ በጣሊያንም ወረራ ጊዜ ባንዳ ሲርመሰመስ የታየ ነው። ከዚያም ወዲህ ቢሆን ሀገሬ ህዝቤ ብለው የተነሱት ብዙሀን አልነበሩም። ግን በትግሉ ውጣ ውረድ፣ መከራን ተቀብለው፣ ህይወታቸውን ገብረው ሌሎችን ሊያፈሩ ችለዋል። አርአያዎች ያስፈልጋሉ፣ ስለ ትግል የሚያወሩት ሳይሆኑ ትግልን ታግለው በተግባር አሳይተው የሚያታግሉት መበርከት አለባቸው። ትግልን በሹመት ብቻ ካየነው፣ ሞታችሁ ለስልጣን አብቁን ከሆነ አቅዋማችን፣ እናንተ ታገሉ እኛ ራቅ ብለን ኑሮአችንን እንግፋ ከሆነ እምነታችን ታጋይ ሳንሆን አስመሳይ መሆናችን ነው። በትግሉ ሜዳ በአቅማችን ደረጃ፣ ልናደርግ በምንችለው ደረጃ የየበኩላችንን አስተዋፅዖ በማድረግ ለሀገራችን አለና ልንላት ይገባል።

የትግል ካርታ ወይም ይዘት አቅጣጫናን ውሳኔ በተመለከተ ለአንዴም ለሁሌም የሚገባል ውሳኔ የለም። ለቀውጢ ሁኔታ የሚተለም ይኖራል። ለተለየ ሁኔታ የሚወሰን ደግሞ ይኖራል። ሁኔታው እየተጤነ ወይም መንገዱ እየታየ ጉዞው ይስተካከላል ማለት ነው። ወጣም ወረደም ግን ምን ቢሆን ምን ያለውን አገዛዝ በህዝባዊነት ፈርጆ እንቀፈው ወይም እንተባበረው ሊከሰት አይገባም። በሰላምና በምርጫ መንገድ የተደረገው ትግል ቢያንስ የወያኔን መሸነፍ አሳይቷል። ግን ይህን የህዝብ ውሳኔ ወያኔ ያከብራል የሚለው ብዥታ የተሳሳተና ጎጂ ለመሆኑ ዛሬ በግልፅ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው። ወያኔ ዛሬ የተቃዋሚ መሪዎችን በእስር እያቃየ፣ ብዙ ሺዎችን

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

በማጎሪያዎች አፍኖ እየበደለ ባለበት ይቅርታ እንጠይቃለን የሚል ሰነድ ፈርሙ በሚል ተፅዕኖ በታሩት ላይ እያደረገ ነው። ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሃቅ የተባለ የባዕድ ቅጥረኛና ፀረ ኢትዮጵያ ግለሰብ ይህን የወያኔ ግብ ለማሟላት እየተሯሯጠ መሆኑም ታውቋል። ለህዝብ የገቡትን ቃል ኪዳን ያልረሱት ይህነ የወያኔን አዋራጅ ሰነድ ለመፈረም እሺ አይሉም የሚል ተስፋ አለ ። ከፈረሙ ግን ይህን ውርደት ድል አስመሰሎ ማቅረብ የሚቻል አይደለም። ከ 200 በላይ ዜጋን ጨፍጭፎ፣ ብዙ ሺዎችን በዴዴሳና ዝዋይ ወዘተ  አሰቃይቶ፣ የተቃዋሚ ድርጅት መሪዎችን በቃሊቲ አግቶ የቆየውን ወንጀለኛ ቡድን ያጠፋነው እኛ ነንና ይቅር በለን ብሎ መለመኑ ወይም መፈረሙ ሀገርንም ትግልም የሚያዋርድ ነው። የኦነግ መሪዎች ከሀገራቸሁ ውጡ ብሎ ወያኔ ሲወስንባቸው እሺ ብለው ሲቀበሉ የተከተለውን የሀፍረት ስሜት የሚደግም ይሆናል።  ትግል የሚጠይቀው መስዋዕትነትና ዋጋ ሁሌም አለ ። ትግል ካልነ ጦመኛ ነኝና ከመረቁ አውጡልኝ ከስጋው ግን ተዉ አይቻልም። ትግሉ የሚያስከትለውን መከራ ሁሉ ለመቀበል ዝግጁ መሆንን ይጠይቃል። ያለፉት ጀግኖች፣ በጦርና ጋሻ ወይም ውኸግራ ግዙፉን የጣሊያን ጦር የተጋፈጡት አርበኞች ሆኑ ትግሉ ነው ህይወቴ ብለው እየዘመሩ፣ ማን ይፈራል ሞት ብለው እየጮሁ የተሰዉት የኢሕአፓ ጀግኖች እንዳሳዩት ሁሉ ትግሉ ሲመር ይጥመናል በሚል  ግትርና ቆራጥ መንፈስ ጠላትን ይጋፈጧል እንጂ ለራሱ አረመኔ ፍጅት ራስን አጥፊ ብሎ አውግዞ ማረነ ብሎ ምለላ የሚታሰብም መሆን የለበትም። ሕዝባዊ ራዕይን፣ሕዝባዊ ቃል ኪዳንን ያረክሳል።

ቃል ኪዳንን ማክበር፣ እምቢኝ ለጨቋኝ አልገዛምን ማክበር፣ ቀናና ሀገራዊ ራዕይን አሳልፎ አለመስጠት ዜጋን ያስከብራል፣ ሀገርን ያኮራል። ለኢትዮጵያ የሚበጅ ራዕየ አለን። ቢወቀጥ አጥንቴ ቢንቆረቆር ደሜ ይህን ክቡር ራዕይ አሳልፈን አንሰጥም አንክድም ማለት መቻል አለብን።  ለወያኔ አንበረከክም። ወያኔን ለማንበርከክና ለማቸነፍ እንዋደቃለን እንጂ።

ፀረ ወያኔ ትግላችን ይፋፋም!!

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com